# መመሪያ ቁጥር 216/2013

## ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ግብር <u>የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ</u>

ንፋስ አመጣሽ ገቢ ነው ሊባል የሚችለው ገቢ፣ በዚህ ገቢ ላይ ሊከፈል የሚገባው ግብር መጠን እና ግብሩ ሥራ ላይ የሚውልበት ቀን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወሰን በገቢ ግብር አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተወሰነው የብር የምንዛሪ ተመን ለውጥ ምክንያት ባንኮች ባገኙት የሥራ እንቅስቃሴያቸው ውጤት ያልሆነ ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ግብር ማስከፈል አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር 693/2003 አንቀጽ 38 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ «ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ግብር የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 216/2013» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2 <u>ትርጓሜ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም «ባንክ» ማለት የባንክ ሥራ እንዲሠራ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም የመንግሥት ባንክ ነው።

## 3. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እ.ኤ.አ. ሰፕቴምበር 1 ቀን 2010 ባደረገው የብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ይሆናል፡፡

## 4. የግብሩ ማስከፈያ ልክ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እ.ኤ.አ. ሰፕቴምበር 1 ቀን 2010 ባደረገው የብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ማናቸውም ባንክ ባገኘው ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ 75% (ሰባ አምስት በመቶ) ግብር ይከፈላል፡፡

## 5. የግብሩ ስሌት መሠረት

በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚከፈለው ግብር ስሌት መሠረት የሚሆነው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተላከው ሪፖርት የተመለከተው እ.ኤ.አ. ሰፕቴምበር 1 ቀን 2010 በተደረገው የብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ባንኩ ያገኘው ንፋስ አመጣሽ ገቢ መጠን ሲሆን፣ የብር የምንዛሪ ተመንን የተረጋጋ ለማድረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በዓመቱ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ማስተካከያ የተገኘውን ገቢ አይጨምርም፡፡

## 6. የመክፈያ ጊዜ

ማናቸውም ባንክ በዚህ መመሪያ መሠረት ግብር ሊከፈልበት በሚገባ ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ግብር እስከ ታህሣሥ 25 ቀን 2003 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ገቢውን አስታውቆ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

7. <u>*የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት*</u>

*የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥለጣን፣*

1. በዚህ *መመሪያ* በተመለከተው *መሠረት* ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ተገቢውን ግብር ይሰበስባል፡፡

2. ከንፋስ አመጣሽ ገቢ የተሰበሰበውን ግብር የሚያሳይ *ሪፖርት* በየወሩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

8. <u>*የመተባበር ግዴታ*</u>

*የኢትዮጵያ* ብሔራዊ ባንክ ባንኮች በብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ያገኙትን ገቢ የሚያሳይ *መረጃ* ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

9. <u>*ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን*</u>

ይህ *መመሪያ* ከህዳር 25 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

***አዲስ አበባ ህዳር 23 ቀን 2003 □ም***

***ሱፍያን አህመድ***
***የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር***